# ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር - አፈርኩብዎ

ወንድሙ መኰንን




ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ. ም በፓርላማ ያደረጉትን ንግግር፤ እያቅለሸለሸኝም ቢሆን ሰማሁት። መስማት ጆሮ ቢያቆሽሽ፤ የኔ ጆር ተጠርጎም ባልጸዳ ነበር። ወቸው ጉድ! ጆሮ አይሰማው የለም አሉ። ድርጅትዎ፤ ዋላታ የመረጃ (ማዛቢያ) አገልግሎት (Walta (mis)Information Service): ታሪካዊውን ንግግርዎን ቀርጾ አሰማን። "ጆሮ ለምን አታድግም" ቢሉት፤ "ይኸን ጉድ እየሰማሁ እንዴት ብዬ ልደግ" አለ አሉ።

መቸም እርስዎን የመሰለ ዋና ሰቆቃ (Prime Misery) እግዚአብሔር ለአገሪቱ መዳረጉ፥ ኢትዮጵያ ምን በድላ ይሆን፤ ምን ኃጢአት ሠርተን ይሆን ያሰኛል። "ጠቅላይ ሚኒስቴር" አሉን?

ከተናገሩአቸው ቃላት፤ አንዳችም የምትወድቅ አትገኝም። እያንዳድንዱ ተመዝግቦ ለታሪክ የሚቀመጥ፤ የአምባገነን ዛቻ፤ ያደገኛ ቦዘኔ ስድብ የተሞላበት አሳፋሪ የፓርላማ ዲስኩር ነበር።

እኔን ያስደነገጠኝ እና የሰቀጠጠኝ አምስተኛው ክፍል ላይ ስደርስ ነበር። እንደ ልማድዎ የቅንጅት መሪዎችን ሲገሽልጡ፤ ብዙ ብዙ ቀሽት የሚያደብኑ አባባሎችን ሰንዝረዋል። ከቅንጅት መሪዎች ጋር እንደማይደራደሩም ዝተዋል። እንኳን ከዛተ ከወረወረም አምላክ ያድናል እንጂ፤ ዛቻዎስ ገድብ ያለፈ ነበር። እዚህ ላይ ከገረመኝ ነገር ውስጥ "በሕግ የበላይነት ላይ ድርድር የለም… ድርድር ማድረግ የሚቻለው፤ በሁለት ነጻ ሰዎች መሀል ነው። አንዱ ወንጀል ሠርቶ ታሣሪ፤ ሌላው አሣሪ ሲሆን በዚያው በሕጉ መሰረት ዋጋውን ያገኛል እንጂ መደራደር አይኖርም" ያሉት ምንኛ ትዕቢት እንደወጠረዎት ያሳያል። መቸም በሰፈሩት ቁና መሰፈርዎ አይቀርምና ግፍዎን አንድ ቀን እርሶም በተረዎ ስለሚያገኙት በይበልጥ ይግፋበት። እኔን በጣም የሰቀጠጠኝ የሚከተለው ንግግሮዎ ነበር።

> *"የተከበሩ አቶ ቡልቻ እንደሚያውቁት ከየትኛውም አገር የምናገኘው ዕርዳታ በባጀት ይንጸባረቃል። ብድርም ከሆነ በብድር ስምምነት ይንጸባረቃል - እዚህ ፓርላማ ይገባል። ፓርላማ የማያውቀው ብር የለም። የምናገኘው ብር በሙሉ በፓርላማ በኩል ያለፈ ነው (እዚህ ላይ በአሽቃባጭዎችዎ ተሳቀልዎት)። ስለዚህ እርስዎ ከሚያውቁት*

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*በላይ የማውቀው ነገር የለም - በዚህ ጉዳይ ላይ። የአሜሪካ መንግሥት በርግጥ ዕርዳታ ይሰጠናል - በተለያየ ዘርፎች። ይኸንን ዕርዳታ ያው እርስዎ ያውቁታል፤ አሁን ባጀቱ ላይ ይንጸባረቃል ብዬ እገምታለሁ። ሶማሊያን በተመለከተ እስካሁን ድረስ ዜሮ አምስት ሳንቲም አልሰጡንም ያልኩት አሁንም ያለ ነገር ነው። መረጃ ላይ እንደጋግፋለን። መረጃ ይሰጡናል፤ መረጃ እንሰጣቸዋለን። ከዚያ አልፎ ግን ዜሮ አምስት ሳንቲም አልሰጡንም በሶማሊያ ጉዳይ የሚለው ግን አሁንም ያለ ነው። ይኸ ማለት የሰንዴ ዕርዳታ አልሰጡንም ማለት አይደለም። በአገር ውስጥ የድርቅ ችግር ለመፍታት። ኤች አይ ቪ ላይ ገንዘብ አልሰጡንም ማለት አይደለም። እሱ በሌላ ፕሮግራም የተያዘ ነው። ኮንዶም ይዘን ሶማሊያን አንዋጋም መቾም።"*

ምነው ጠቅላይ ሚኒስቴር! ጠቅላይ ሚኒስቴርነትዎን ረሱት እንዴ? ያሳደጎዎትን በሕይወትዎ አንዲት ጊዜ እንኳን በመልካም አንደበትና ምግባር ስማቸውን ቢያስጠሩ ማን አለበት? የሚያሳድጉአቸውን ልጆችዋን ርሱአቸው እንዴ! ስለርስዎ አፍሬ መደበቂያ አጣሁ! በዕውነት በጣም አፈረኩልዎት! የጫትና የሲጃራ መነሃሪያ መሆኑ አንሶት፤ ከአፍዎ የሚወጡት ቃላት ከኢትዮጵያ አልፈው በስደት በየተደበቅንብት መንደርና ከተማ ሁሉ ብክለት እየፈጠሩ ጤና እየነሱን ነው።

ለመሆኑ "ኮንዶም ይዘን ሶማሊያን አንዋጋም" ብለው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና "የፓርላማ" እሥረኛ ላደረጉአቸው ግለሰቦች መደስኮርዎ አዋቂነትዎን ነው የሚያሳየው ወይንስ አወቅሽ አወቅሽ ስትባል መጽሐፍ እንዳጠበችው ዓይነት ግብዝ መሆንዎን ነው? እንደዕውነቱ ከሆነ እንዲህ ዓይነት የኮንዶም ቀልድና ጨዋታ ከባለቤትዎ ባይዘል ይሻል ነበር። የፓርላማ ምክትል አፈጉባዔ የሆኑት ወይዘሮ፤ እጅግ ከማፈራቸው የተነሳ እየተቁነጠነጡ በመዶሻቸው ጠረጴዛውን እየደበደቡ ሥነ-ምግባር ሊያስከበሩ በሳቁት ላይ ሁሉ ተግጻጽ አወረዱ። እርስዎንማ ሥነ-ምግባር የለሹን የፓርላምዋን ባለንብረት ማን ሊገስጽ ይዳዳዋል?

"ኮንዶም ይዘን ሶማሊያን አንዋጋም" ማለትዎን ሶማሌዎች ሁሉ መስማታቸው አይቀሬ ነውና፤ ሀገራቸውን የወረረውን ጋጠ-ወጥ ሽብርተኛ ማንነት የበለጠ ለመረዳት እንድሚያስችላቸው ብዙም አያጠራጥርም። እኔ ገን የበለጥ አፈርኩብዎ እንጂ ሳቅም አይዳዳኝ።

ምነው ቢያንስ እግዚአብሔር ከርስዎ እስኪገላግለን ለልጆችዋና እርስዎ የተናገሩትን ሁሌ እንደ በቀቀን በዕብሪት ለሚደጋግሙብን እንደነበረክት ስምዖንና ስብሀት ነጋ ዓይነቱ በለሥልጣናት የበለጠ ብልግና ባያስተምሩብን! እባክዎን ለዚህ አደገኛ አፍዎ ለከት ያበጁለት።

እስቲ ለማንኛውም "ንግግርዎን" መልሰው ያዳምጡ።

http://www.waltainfo.com/CurrentIssues/2007/Jun/meles.htm
http://addisvoice.com/audio/zenawi_joking.mp3 (clip)

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com